የተከበራችሁ የአገራችን ህዝቦች!

የአገራችን ህዝቦች የመሬታቸውና የምርታቸው ነፃ ተጠቃሚዎች ለመሆን፣ የብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸውን እድል በራስ የመወሰን መብት እንዲከበር፣ የዜግነት መብቶች የተከበሩበትና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲመሰረት በተለያየ አግባብ ሲያካሂዱት የኖሩት ህዝባዊ ትግል በአምባገነኑ የደርግ መንግስት መገርሰስ ድል ለተቀዳጀበት የግንቦት ሃያ 17ኛ አመት በአል እንኳን አደረሰን እያለ ኢህአዴግ የተሰማውን ደስታ ይገልፃል፡፡

የዘንድሮ ግንቦት ሃያ በአል አገራችን ሁለተኛውን ሚሌኒየም አገባዳ ሶስተኛውን በተቀበለችበትና የአገራችንን ህዳሴ በሁሉም መስክ ለማጎልበት መላው ህዝባችን በመረባረብ ላይ በሚገኝበት ወቅት የሚከበር መሆኑ የተለየ ያደርገዋል፡፡ አገራችን እስከ አስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ገደማ በስልጣኔ ተራምደዋል ከሚባሉት አገሮች ጎራ የምትመደብ የነበረች ቢሆንም ከዚህ ወቅት ጀምሮ ግን በውስጧ በነበረው የአስተዳደር ችግር ምክንያት ወደ ፊት መራመድ ተስኗት ቆይታለች፡፡ በመሆኑም ከእኛ ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ የነበሩት ብቻ ሳይሆን ከኋላችን የተነሱትም ቀድመውን ሲበለፅጉ የእኛ እጣ ፈንታ በድህነት መማቀቅ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በተለይም ደግሞ በአገራችን የተማከለ አስተዳደር ከተመሰረበት ካለፈው ክፍለ ዘመን መባቻ ጀምሮ አገራችን አስከፊ ብሄራዊ ጭቆና በመንሰራፋቱና ፀረ ልማት በሆኑ መንግስታት ስር በመውደቋ እድገቷ መገታት ብቻ ሳይሆን ህልውናዋም ለከፍተኛ አደጋ ተጋልጧል፡፡ ይህ ሁኔታ መቀየር የጀመረው መላ የአገራችን ህዝቦች አምባገነናዊውን አገዛዝ በትጥቅ ተፋልመው ግንቦት 20/1983 ከገረሰሱት በኋላ ነው፡፡ እነሆ ከግንቦት/83 ወዲህ ባሉት 17 አመታት አገራችን በለውጥና እድገት ምህዋር ውስጥ ገብታ በመገስገስ ላይ ትገኛለች፡፡

ይህንን መነሻ በማድረግም ነው የዘንድሮውን በአላችንን «ግንቦት 20 የኢትዮጵያ ህዳሴ መሰረት» በሚል መሪ ቃል የምናከብረው፡፡ በርግጥም በግንቦት 20 ታላቅ ህዝባዊ ድል አገራችን ወደ አዲስ መድረክ ገብታለች፡፡ የአገራችን ህልውና የተመሰረተባቸውን የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት ጥያቄዎች በአግባቡ በመመለስና አገራችንን ከኋላቀርነትና ድህነት በማውጣት እንደገና ወደስልጣኔ፣ እንደገና ወደታላቅነት እንድትገባ መንገዱ በግንቦት 20 ተጠርጓል፡፡

የዘንድሮው ግንቦት 20 የሚከበረው በአገራችን ለሶስተኛ ጊዜ የተካሄደው የአካባቢ አስተዳደር ምርጫ በላቀ የህዝብ ተሳትፎ፤ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ

አግባብ በተጠናቀቀበትና የልማትና መልካም አስተዳደር ጥረቶቻችንን ውጤታማ ለማድረግ ቁልፍ ሚና ያላቸው የወረዳ፣ የከተማና የቀበሌ አስተዳደሮች በአዲስ መንገድ እየተዋቀሩ በሚገኙበት ወቅት መሆኑ ሌላው በአላችንን የተለየ የሚያደርገው ጉዳይ ነው:: በዚህ አጋጣሚም በሚያዝያ ወር በተካሄደው የአካባቢና የማሟያ ምርጫ መላ የአገራችን ህዝቦች የኢህአዴግና የአጋሮቹን እጩዎች በመምረጥ፣ እንድናስተዳድረው ይሁንታውን ስለሰጠን ኢህአዴግ ምስጋናውን ያቀርባል::

**የተከበራችሁ የአገራችን ህዝቦች!**

የኢትዮጵያ ህዝቦች ቀደም ሲል የፊውዳሉን ስርአት፣ ኋላም ዘውዳዊውን አገዛዝ ተክቶ ወደ ስልጣን የመጣውን የደርግ መንግስት ወቅቱ በጠየቀው የትግል አግባብ ሁሉ በፅናት ታግለዋል:: በተለይም ደግሞ በአፍሪካ በግዙፍነቱ ተወዳዳሪ ባልነበረው የአፈና ተቋም በአገራችን ህዝቦች መብት ላይ የዘመተውንና ሃብትና ንብረታቸውን ወርሶ ለድህነት የዳረጋቸውን የደርግ አምባገነን መንግስት በትጥቅ ትግል ሳይቀር ተፋልመዋል:: በዚህ ትግል በከተማና በገጠር እጅግ በርካታ የህዝብ ልጆች ክቡር መስዋእት ከፍለዋል:: በአገራችን የአምባገነንነትን ምእራፍ ለመጨረሻ ጊዜ የዘጋውን የግንቦት ሃያ ድል እውን ለማድረግ ክቡር መስዋእት የከፈሉ መላ የአገራችን ህዝቦች ለታላቁ ገድላቸው ሊመሰገኑ ይገባል:: መላ የአገራችን ህዝቦች በትግላቸው በአምባገነንነት ላይ ግንቦት ሃያ የተጎናፀፉት ድል በፀረ ድህነትና ኋላቀርነት ትግሉ በድል አድራጊነት እንዲወጡ አስተማማኝ መነሻ ነው ብሎ ኢህአዴግ ይወስዳል:: በዚህ የአገራችን ህዝቦች ታሪክ ሰሪነት በመተማመንም በፀረ ድህነትና ኋላቀርነት ትግሉ ባለፉት 17 አመታት እንዳደረገው ሁሉ ከስ የሚጠበቀውን ለመወጣት ዝግጁ እንደሆነ በድጋሚ ያረጋግጣል::

ባለፉት 17 አመታት አገራችንን በሁሉም መስክ ለመለወጥ የሚያስችሉ ስርነቀል እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል:: የአገራችን ህልውና ከሰላም ጋር በጥብቅ የተቆራኘ በመሆኑ አስተማማኝ ሰላም ለማረጋገጥ የተደረጉት ጥረቶች ውጤታማ ሆነዋል:: የብሄር ብሄረሰቦች የሃይማኖቶች፣ የፆታ እኩልነት ህገ-መንግስታዊ ዋስትና እንዲያገኙ ተደርጓል:: ብዙህነትን የተቀበለና በየጊዜውም እየጎለበተ በመሄድ ላይ የሚገኝ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በመገንባት ላይ እንገኛለን:: በማሽቆልቆል ሂደት ላይ ይገኝ የነበረውን የአገራችንን ኢኮኖሚ ከውድቀት እንዲያገግም ብቻ ሳይሆን በተለይም

ባለፉት አምስት አመታት በተከታታይ ከአስር በመቶ በላይ እድገት እንዲያስመዘግብ ማድረግ የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በአጠቃላይም ከግንቦት 1983 በፊት የነበሩ አገራዊ ቀውሶች ተወግደው በለውጥ ጎዳና መራመድ የጀመረች ብሩህ ተስፋ የፈነጠቀባት ኢትዮጵያን ለማየት በቅተናል፡፡

ለሁላችንም ግልፅ እንደሆነው አገራችን የምትመራበት ህገመንግስት ከፀደቀ በኋላ በአገራችን የሚገነባው ስርአት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ባህሪያት በማያሻማ አኳኋን ተመልሰዋል፡፡ በተለይም በ1993 ከተደረገው የድርጅታችን የተሃድሶ ንቅናቄ በኋላ በመሰረታዊ የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት ጉዳዮች ላይ የምንመራባቸው ፖሊሲዎችና ስትራተጅዎች ጠርተውና ተዘርዝረው እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ እነዚህ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች ባለፉት አመታት በተግባር ተሞክረው ትክክለኛና ውጤታማ መሆናቸውም ተረጋግጧል፡፡ ህገመንግስታችንና ፖሊሲና ስትራተጅዎቻችን ለመተግበር በተደረገው ጥረት በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የህዝቦች አንድነት ይበልጥ እየጎለበተ ዜጎች በህገመንግስታዊ መብቶቻቸው እየተጠቀሙ በመሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ በመላ የአገራችን ገጠሮችና ከተሞች የልማት ቋያ ተቀጣጥሏል፡፡ በዚህም የገጠር ልማት ስትራተጂያችን የግብርናችንን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ፣ ከእጅ ወደ አፍ ከሆነው የአመራረት አግባብ ወደ ኮሜርሻላይዜሽን በመሸጋገር መዋቅራዊ ለውጥ እያመጣ ይገኛል፡፡ የከተማና የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂያችንም ከፍተኛ ለውጥ ማስመዝገብ ጀምሯል፡፡

በአሁኑ ወቅት ኢህአዴግና በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት የሚጠብቋቸው ዋነኛው ተግባራት ባለፉት አመታት ከነበሩት በአይነቱ የተለየ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት በልማቱም ሆነ በመልካም አስተዳደር መስክ የወጡት ፖሊሲዎችና ስትራተጅዎች እንዲሁም የማስፈፀም አቅጣጫዎች ጥቂት በማይባሉ ቦታዎች ውጤታማ ሆነዋል፡፡ ቀጣዩ የቤት ስራ እነዚህን ወደ ሁሉም የማስፋፋት ጉዳይ ሆኖ ይገኛል፡፡ በየአካባቢውና በየመስኩ የሚታዩትን መልካም ልምዶች በፍጥነት ወደ ሌሎች ማስፋፋት፣ በሁሉም ደረጃና አካባቢ የፈፃሚ አካላትን ተነሳሽነትና የመፈፀም አቅም ማሳደግ፣ ሁሉም ዜጋ በየተሰማራበት መስክ ውጤታማ ሊሆን ይችል ዘንድ አስፈላጊውን አመራርና እገዛ በመስጠት ውጤታማ አሰራሮች የሁሉም እንዲሆኑ መረባረብ ዋነኛው ተግባራችን ተደርጎ ተወስዷል፡፡

ይህንን መሰረት በማድረግም ኢህአዴግ በቀጣዮቹ አመታት የግብርናውን ምርታማነት ለማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በተናጠል አርሶአደሮችና አካባቢዎች ደረጃ የተገኙ ስኬታማ የአመራረት ልምዶችን ወደሁሉም በማስፋፋት ከያዝነው አመት

ጀምሮ በግብርናችን ምርታማነት ላይ ጉልህ ለውጥ ለማምጣት ርብርብ ይደረጋል። በከተሞች በአነስተኛና ጥቃቅን ስራዎች የተገኙትን መልካም ልምዶች በመቀመር ነባሮቹን የማጠናከርና አዳዲሶችን ደግሞ የማስፋፋት ስራ በትኩረት ይከናወናል። በመኖሪያ ቤት ልማት በኩል በትላልቆቹ የአገራችን ከተሞች በተጀመረው ስራ እስካሁን የተገኙትን መልካም ልምዶች በማስፋፋት በከተማም በገጠርም የመጠለያ ችግርን ለመቅረፍ የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ለማካሄድ ተዘጋጅቷል። በመሰረተ ልማት መስክ በተለይም የመብራትና የስልክ አገልግሎትን ወደገጠር ቀበሌዎች የማስፋፋትና በከተሞቹም አገልግሎቱን በጥራት የመስጠት ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል። ትምህርትን በማስፋፋት መስክ የተመዘገቡት ውጤቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ በዋነኛነት ደግሞ የትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ይደረጋል። በጤና ጥበቃ በኩል በተለይም በመከላከል መስክ የተጀመሩት ስራዎች ጥራትና ስፋታቸው ተጠብቆ የሚቀጥሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ትኩረት ይሰጣል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የተጀመሩት ጥረቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ የኢንቨስትመንት ፍሰቱን የሚያደናቅፉ ችግሮችን ያለማቋረጥ ለመፍታት ቀጣይ ጥረት ይደረጋል። በመንግስትና በግሉ ሴክተር መካከል የተጀመረው መልካም ግንኙነት እንዲዳብር ይደረጋል። የነዚህ ሁሉ ጥረቶች ድምር ውጤትም በተለይም በከተሞች ያለውን የስራ አጥነት ችግር የማቃለል ሚና እንደሚጫወት ይታመናል።

እነዚህ የልማት ርብርቦች የአገራችንን ኢኮኖሚያዊ እድገትና የህዝቡን ተጠቃሚነት አሁን ከሚገኝበት ከፍ ወዳለ ደረጃ እንደሚያሸጋግሩት ይታመናል። በአገራችን ለዘመናት ስር ሰደው የቆዩት ችግሮች በአንድ ጀንበር እንደማይፈቱና በተለያዩ ምክንያቶችም አዳዲስ ችግሮች እንደሚከሰቱ ኢህአዴግ ይገነዘባል። ከዚህም በመነሳት ከዚህ በፊት እንዳደረገው ሁሉ ነባርም ሆኑ ጊዜያዊ ችግሮች በህዝባችን ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ደረጃ በደረጃ ለማቃለል ኢህአዴግና በእሱ የሚመራው መንግስት አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ጥረት ያደርጋሉ። በአሁኑ ወቅት በከተሞች የሚገኘውን ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ክፉኛ የሚፈታተነው የኑሮ ውድነት ሆኗል። ኢህአዴግና መንግስት የወቅቱ ዋነኛ ጠላት የዋጋ ግሽበት እንደሆነ አረጋግጠው ይህንን ሊያቃልሉ የሚችሉ የተቀናጁ ርምጃዎች ሲወስዱ ቆይተዋል። ካሁን በኋላም ችግሩ አስተማማኝ መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ ጥረት ማድረጋቸውን ይቀጥላሉ።

ልክ እንደልማቱ ሁሉ የህዝባችን ቀዳሚ ጥያቄ የሆነውን የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ለመፍታትም ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። በዚህም ሂደት መልካም ውጤት

የተገኘባቸው አፈፃፀሞች ታይተዋል፡፡ ኢህአዴግ በዚህ ረገድ ቀጣዩ ስራ የተገኙ መልካም የአፈፃፀም ልምዶችን ቀምሮ በሁሉም አካባቢ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግና የህዝባችንን የመልካም አስተዳደር ጥማት ማርካት ነው ብሎ ያምናል፡፡ በአሁኑ ወቅት በመላ አገራችን መንግስትና ህዝቡ በሚያደርጓቸው የተቀናጁ እንቅስቃሴዎች አስተማማኝ ሰላም ሰፍኖ ይገኛል፡፡ ሰላማችንን ይበልጥ ማጎልበት በቀጣይም የላቀ ትኩረት እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና ሰላምን የማስፈን ተግባሮቻችን በተሟላ መንገድ ሊተገበሩና ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት ህዝባችን በንቃት ሲሳተፍባቸው እንደሆነ በማመን ድርጅታችን ለህዝብ የተደራጀ ተሳትፎ መዳበር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል፡፡

በመጨረሻም ግንቦት 20 የአገራችን ህዳሴ መሰረት በሚል መሪ ቃል ግንቦት ሃያን ስናከብር መላ የአገራችን ህዝቦች ኢህአዴግና መንግስት የያዟቸውን ቀጣይ የልማትና የመልካም አስተዳደር ግንባታ ግቦች ለማሳካት እንዳለፉት አመታት ሁሉ ዛሬም ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ኢህአዴግ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ በተለይም ደግሞ ወጣቱ ከሱ በፊት የነበረው ትውልድ በወቅቱ የነበረውን አስከፊ ብዝበዛና ጭቆና ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍሎ እንዳስወገደው ሁሉ ድህነትንና ኋላቀርነትን ለማስወገድና ብልፅግናና ዴሞክራሲን ለማስፈን በሚካሄደው ትግል ከመቸውም ጊዜ በላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆንና አገር ተረካቢነት ተልእኮውን በአግባቡ እንዲወጣ ኢህአዴግ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አገራችንን ከድህነትና ኋላቀርነት የማላቀቅ፣ ልማትና ዴሞክራሲን የማረጋገጥ ተግባር የተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል ግዴታም መብትም አይደለም፡፡ ይልቁንም ሁሉንም የአገሪቱን ዜጎች የሚመለከት የጋራ ተልእኮ እንደሆነ ኢህአዴግ አበክሮ ያምናል፡፡ በዚህም በፖለቲካ አስተሳሰብ፣ በእምነትና በመሳሰሉት ያሉ ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የጋራችን የሆነችን አገር በጋራ ለመገንባት በመቻቻል፣ ጥቅሞችን በማጣጣምና የህግ የበላይነትን በማስከበር ዴሞክራሲያዊ መርሆዎች እየተመራን አገራችንን ለመገንባት በጋራ እንድንቀሳቀስ አገራችን በጀመረችው የለውጥ ሂደት ገንቢ አስተዋፅኦ ለማድረግ ለሚፈልጉ ሃይሎች ሁሉ ኢህአዴግ ጥሪ ያቀርባል፡፡

አዲሱ ሚሌኒየም በርግጥም የኢትዮጵያ ህዳሴ ይሆናል!

ዘላለማዊ ክብር ለግንቦት ሃያ ድል ያበቁን ሰማእታት!